**ሳምንታዊ ዜና (መጋቢት 28 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**የአዲስ አበባ ጊዜያዊ ባለአደራ ባለሥልጣናት በምንም ዓይነት ወንጀል እንዳይጠየቁ መለስ ትዕዛዝ አስተላለፈ፣ ወያኔ በፍርሃት 28 የአውሮፕላን ጠለፋ ተከላካዮች ለጥበቃ አሰማራ፣ ከውስጣቸውም 26ቱ የትግራይ ተወላጆች፣ 2ቱ የኦሮሞ ተወላጅ ናቸው፣ ወያኔ ሱማሌ ከአዘመታቸው 4ቱን ረሸነ፣ የእሳት ቃጠሎ አሁንም ቀጥሉዋል፣ በርካታ ወታደሮች ስርዓቱን በመክዳት እየኮበለሉ ነው፣ አሜሪካ ድንገተኛ ጥሪ ለዜጐቿ አስተላለፈች»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ያንብቡ …………..

ወያኔ ዙሪያውን አንደብራና ተወጥሮ ባለበት በዚህ ወቅት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ ከታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ውጊያ ማድረጉን ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ረቡዕ መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም ከአዲስ አበባ በግምት 450 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ገዋኔ ተብላ በምትጠራው አካባቢ የወያኔ ጦር እና በአካባቢው ከሚንቀሳቀስ ታጣቂ ኃይል ጋር ውጊያ አድርጐ ከፍተኛ ኪሣራ የደረሰበት መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

በተደጋጋሚ ጊዜ በጅቡቲ መስመር ላይ ከታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ከፍተኛ ውጊያ እየገጠመ ያለው ወያኔ በቅርቡ በገዋኔ አቅራቢያ ድንገተኛ ጥቃት በታጣቂ ኃይሎች ተሰንዝሮበት ከ4 በላይ ወታደሮች ተገድለውበት በርካቶች ቆስለውበት እንደነበር የጠቀሰው ይኸው የደረሰን ዘገባ በወቅቱ ታጣቂዎቹ የወያኔ ወታደሮች የፀሀዩን ሙቀት መቋቋም አቅቷቸው በመጠለያቸው ውስጥ እረፍት ላይ እንዳሉ አደጋ የጣሉባቸው ሲሆን፣ ድርጊቱን ፈፅመው ወደ ጅቡቲ መስመር የተገዳዙ መሆኑንም ዘገባው በዝርዝር አስረድቷል፡፡

በዚህም ውጊያ የተነሳ በአካባቢው ምንም አይነት የመኪና እንቅስቃሴ እንዳይኖር ተደርጐ በማግስቱ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም ጉዞ የተጀመረ ሲሆን እንቅስቃሴው በወታደራዊ ውጠራ እንደሆነም ዘገባው አብራቷል፡፡

በአሁን ሰዓት ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚመጡና ወደ ጅቡቲ ለሚጓዙ አሽከርካሪዎች ከፍተኛ ስጋት የፈጠረባቸው ከመሆኑም በላይ ቀድሞ ሲጓዙበት ከነበረው ቀናት በላይ በችግሩ ምክንያት እያረዘሙ ለከፍተኛ ወጪ እየተዳረጉ እንደሚገኝ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ወያኔ የረባ ተቃዋሚ የለኝም እያለ በሚለፍፍበት በዚህ ወቅት ተቃዋሚ በወንበር ሳይሆን በመሳሪያ ነው በማለት ዙሪያውን እንደ ብራና ወጥረው ባገኙ ት አጋጣሚ ሁሉ ጥቃት እየሰነዘሩበት ሲሆን፣ በተለይ በዚህ በአፋር ክልል ውስጥ

በተደጋጋሚ ግዜ ድንገተኛ ጥቃት እየሰነዘሩበት እንደሚገኝ ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ትዝብታቸውን በአንክሮ ይገልፃሉ፡፡ በገዋኔ አካባቢ ስለደረሰበት ድንገተኛ ጥቃት የወያኔ ቡድን አንዳችም ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን፣ ምናልባትም በቅርቡ በተቀነባበረ ፊልም ጥቃት አድርሻለሁ ብሎ እንደለመደው ተራና የውሸት ፕሮፓጋንዳ ለማቅረብ ይችላል ተብሎም ይጠበቃል፡፡

የወያኔው ቡድን ሁሉን ለእኔ ብቻ ማለቱን ቀጥሎበት ቀድሞ ያወጣውን መመሪያ አንደገና በማጠንከር ሰሞኑን አዲስ መመሪያ ማውጣቱን የከባድ መኪና ባለቤቶች ገለፁ፡፡

እንደነዚሁ ወገኖች ገለፃ ከሆነ በአሁን ሰዓት አንድ ከባድ መኪና ለመግዛት ከ1- ሚሊዮን ብር በላይ የሚፈጅ ሲሆን ይህንን መኪና ካስገባ በኋላ በሀገሪቷ በሚገኙ የመኪና አካል መገጣጠሚያዎች ማሰራት የሚችል ቢሆንም ወያኔ አዲስ ስልት ባወጣው መሠረት ግን በመስፍን ኢንጂነሪንግ ካላስቀጠቀጠ ወደ ስራ ማሰማራት እንደማይቻል ገልፀዋል፡፡

ወያኔ በፖለቲካው በኩል በመሣሪያ ኃይል የበላይነቱን ተቆጣጥሮ እንዳለው ሁሉ በኢኮኖሚውም የበላይነቱን ለመያዝና የወያኔን ባለሥልጣናት ኪስ ለማደለብ ሲባል ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የጭነትም ሆነ የነዳጅ መኪኖች በግዳጅ የሚቀጠቀጡት መቀሌ ድረስ ሄደው መስፍን ኢንጂነሪንግ ነው በማለት ያስገደደ ሲሆን፣ በርካታ የግል ባለሀብቶች በሀገራችን ውስጥ የፈለግነው ቦታ ማስቀጥቀጥ አንችልም ወይ እያሉ እያማረሩ እንደሚገኙም ከባለሀብቶቹ ገለፃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተለይም በአሁን ሰዓት እነማሩና ሌሎች በብቃትና በጥራት ከምስራቅ አፍሪካ ተወዳዳሪ ያልተገኘላቸው ድርጅቶች መኖራቸው እየታወቀ መቀሌ ድረስ ሄዳችሁ መስፍን ኢንጂነሪንግ ካላስቀጠቀጣችሁ ወደ ስራ መሰማራት አትችሉም መባሉ በእጅጉ የሚያበግን ከመሆኑም በላይ እንደ ሁለተኛ ዜጋ መቆጠራችን የሚያሳዝንም የሚያሳፍርም ነው ሲሉ እያማረሩ መሆኑን ታውቋል፡፡

በአሁን ሰዓት የአንድ ከባድ መኪና ቦቴ መኪና በግለሰብ ድርጅቶች ለማስቀጠቀጥ 300 ሺህ ብር ሲሆን በመስፍን ኢንጅነሪንግ ግን ደረጃውን ያልጠበቀ፣ በተባለበት ሰዓትና ጊዜ እንኳዋን ሳያደርሱ ከ500 ሺህ ብር በላይ የሚያስከፍል ሲሆን፣ የጭነት መጫኛውንም ለመቀጠቀጥ ደግሞ በግል ድርጅቶች ከ150-200 ሺህ ብር ድረስ የሚያስከፍሉና በተባለበት ቀን አድርሰው በጥራት ሰርተው የሚያስረክቡ ሲሆን መስፍን ኢንጅነሪነግ ግን ከ300 ሺህ ብር በላይ እንደሚያስከፍል እነዚሁ ባለሀብቶች ገልፀዋል፡፡

ለሀገራችን ተስማሚ እና ምቹ ናቸው ተብለው በአውሮፓ የሚሰሩ መኪኖች መሆናቸውን እየታወቀ እነ ወያኔ ከቻይና ጋር በጀመሩት አዲስ ፍቅር ምክንያት

ጥራታቸውና አገልግሎቶታቸው በጣም የወረዱትን መኪኖች ባለሀብቶች በግዴታ ገዝተው እንዲያስገቡ ለማድረግም በጥናት ላይ እንዳሉ የመንገድ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

በቅርቡ በርካታ አይነት የቻይና ገልባጭ መኪኖች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የነበረ ቢሆንም አንድ ወርና ከዚያም በላይ ማገልገል አቅቷቸው በየሄዱበት ተገትረው እየቀሩ መሆኑን በተደረገው ጥናት የተረጋገጠ እንደሆነ ምንጮቹ ጠቁመው ይህንን እያወቁ ወያኔዎች ከቻይና ጋር አዲስ ፍቅር ስለያዛቸው ብቻ ያለሆነ እና ሊሰሩ የማይችሉ መኪኖች ኢትዮጵያውያን ከቻይና ገዝተው እንዲያስገቡ የሚያስገድድ ህግ እየተጠናና እየተዘጋጀ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው በሀገርና በህዝብ ገንዘብ ለመቀለድና ባለሀብቱንም ደሀ ለማድረግ የወያኔ ሩጫ በጣም የሚያሳፍር ነው ሲሉም ተችተዋል::

በቅርቡ ለአዲስ አበባ ከተማ ታክሲ አገልግሎት ይውላሉ ተብሎ ከቻይና ተገዝተው የገቡት መኪኖች ገና ከጅቡቲ ሲነሱ 30 ኪሎ ሜትር መጓዝ አቅቷቸው በየመንገዱ የቀሩ ሲሆን አዲስ አበባ ገብተው ስራ የጀመሩት መኪኖችም አንድ ወር ማገልግል አቅቷቸው ሜክሲኮ በሚገኘው በቀድሞው አንበሳ ጋራዥ ውስጥ ተገትረው እንደሚገኙ እየታወቀ አሁንም ቀድሞ ከገቡት 100 መኪኖች በተጨማሪ ሌላ 100 በድጋሚ ሰሞኑን ማስገባታቸው ታውቋል::

የአዲስ አበባ ጊዜያዊ ባለአደራ ባለሥልጣናት በምንም አይነት ወንጀል እንዳይከሰሱ ሲል መለስ ዜናዊ በምስጢር ትዕዛዝ ማስተላለፉን የመስተዳድሩ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

ገለልተኞች ናቸው ተብለው የተሾሙት የአዲስ አበባ ጊዜያዊ ባለአደራ ባለሥልጣናት ቀድሞም የወያኔ አባሎችና ቀንደኛ አቀንቃኞች እንደነበሩ በየጊዜው ስንገልፅ የነበረ ሲሆን ዛሬ በሰሩት ወንጀል እንዳይጠየቁ መለስ ጥብቅ መመሪያ ማስተላለፉን ከምንጮቹ ገለፃ ለማወቅ ተችሏል::

በተለይም የመለስ ትዕዛዝ ከደረሳቸው ዋና ዋና መስሪያ ቤቶች ውስጥ በመሠረት ታደሰ የሚመራው የማዕከላዊ ምርመራ ዋና መስሪያ ቤት እና የፌደራል ፀረ ሙስና ኮሚሽንን የሚገኙበት ሲሆን፣ እንኩዋን ለመክሰስ ቀርቶ ሌላ ችግር ቢያጋጥማቸው እገዛና ትብብር እንዲደረግላቸውም ጭምር የሚያዝ መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል::

በቅርቡ ይህ ትዕዛዝ ወጪ የሆነበት ምክንያት ምንጮቹ ሲያብራሩ በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦባቸው ምርመራ ተጠናቆ ወደ አቃቤ ህግ መዝገቡ ቢገባም ከመለስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ክሱ የተነሳላቸው ሲሆን በ1994 ዓ.ም በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲቀሰቀስ የመነን ት/ቤት መምህር ሆኖ ሲሰራ የነበረው ሐጉስ የተባለው ግለሰብ የፌዴራል ፖሊሶች በትምህርት ቤት ግቢ

ውስጥ አስገብቶ በርካታ ተማሪዎች እንዲደበደቡ ያደረገ በዚህም ተግባሩ የዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ሆኖ የተሾመ በዚያም ትምህርት ቤት በ1997 ዓ.ም ሰኔ ላይ በየትምህርት ቤቱ በተቀሰቀሰ ተቃውሞ የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪዎችን በሞባይል እየቀረፀ ለደህንነትና ለፌዴራል ፖሊስ በመስጠት በርካታ ተማሪዎችን ያሳፈሰና ያስደበደበ ሲሆን፣ በወቅቱ ተማሪዎቹ ይህንኑ በመረዳታቸው የተነሳ ከፍተኛ ድብደባ አድርሰውበት ሆስፒታል ገብቶ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮች አሁን የጊዜያዊ ባለአደራው ሲቋቋም ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ነፃ ናቸው ተብሎ ከተሾሙት መካከል አንዱ ሲሆን የአዲስ አበባ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ሆኖ የወያኔ ታማኝነቱን እየገለፀ የሚገኝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ምንጮቹ አክለውም በቅርቡ ወደ ኦጋዴን የህዝብና የቤቶች ቆጠራ ከአዲስ አበባ በግዳጅ እንዲዘምቱ ያደረገና አንሄድም ብለው የቀሩትን መምህራኖች ስልጣኑን ተጠቅሞ ከስራ ገበታቸው ላይ ያገዳቸው መሆኑን እና ያባረራቸው ይኸው የህወሓት አባሉ ሀጐስ ከተከሰሱት ውስጥ አንዱ እንደነበር ገልፀው የአዲስ አበባ የጤና ቢሮ ኃላፊዋ የደኢህዴን/ወያኔ አባልና አቀንቃኝ፣ የአዲስ አበባ የመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊው እና ሌሎች 4 የክፍለ ከተሞች የወያኔ አባል ባለሥልጣናት ከህዝብ የዘረፉትን ገንዘብ እንዳይነካባቸው በሚል ከመለስ ከለላ ማግኘታቸውንም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የአዲስ አበባ ጊዜያዊ ባለአደራ አስተዳደር ከንቲባው አቶ ብርሃነ ደሬሳ በዚህ ጉዳይ ላይ ተጠይቀው ማን ምን እንደሆነ አላውቅም ግን ተሹመው ይመጣሉ በማለት እራሳቸውን ጨምሮ ሁሉም የወያኔ ሹመኛ መሆናቸውን በግልፅ ተናግረዋል፡፡

ግራ ተጋብቶ ግራ የሚያጋባው ወያኔ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አካሄዶችንና እርምጃዎችን እየወሰደ ከድጡ ወደ ማጡ እየተዘፈቀ የሚገኝ ሲሆን፣ በዚያው ልክ ደግሞ የፍርሃቱ መጠን እየጨመረ መምጣቱን የተለያዩ ዘገባዎች ገለፁ፡፡

ወያኔ ከፍርሃቱ የተነሳ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ አየር መንገድ በእያንዳንዱ አውሮፕላን ላይ ተመድቦ የሚሰራ አንቲ ሃይጃከር እንዳይኖር አድርጐ የነበረ ቢሆንም በቅርቡ ግን ዙሪያውን በታጣቂ ተቃዋሚዎች በሚሰነዘርበት ጥቃትና በሀገር ውስጥ በደረሰበት የህዝብ ተቃውሞ የተነሳ በፍርሀት አንቲ ሃይጃከር አሰልጥኖ ማሰማራቱን ከአትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን መስሪያ ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

የትግራይ ተወላጅ የሆኑ 26 እና የኦሮሞ ተወለጆች 2 ብቻ በድምሩ 28 የአውሮፕላን ጥቃት ተከላካይ ሆነው የተመደቡ ሲሆን በአንድ አውሮፕላን ላይ

ሁለት ሁለት በመሆን በሀገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ በረራ ላይ እንዲሰሩ መመደባቸውን ከምንጮቹ ገለፃ ለማወቅ ተችሏል።

ደደቢት አመጣሽ የወያኔው ቡድን አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ከገባ ጊዜ ጀምሮ በሀገሪቷ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ በርካታ አውሮፕላኖች ተጠልፈው የተወሰዱና በተለይም በኮሞሮስ ደሴት ላይ ከ127 ሰዎች በላይ አሳፍሮ ህዝብ ያለቀበት ትርኢት የተካሄደበት ወያኔ ባመጣው ጣጣ መሆኑን እነዚህ ምንጮች ገልፀው በየሄድኩበት እኔው ልቆጣጠረው በሚል ሁሉም ቦታ የህወሓት እጅ እንዳለበትና አሁንም ለአውሮፕላን ጥበቃ እንኩዋን ተብሎ ከተቀጠሩት 28 ሰዎች 26 ያህሉ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው የስርዓቱን የስጋት መጠን ያሳያል ሲሉም እነዚሁ ወገኖች ያስረዳሉ።

ወያኔ በዘረጋው የከፋፍለህ ግዛ ፖሊስ ምክንያት ቀድሞ በሲቪል አቪየሽንና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኞች መካከል የነበረ መተባበር፣ መፈቃቀር እንዳይኖር ለማድረግ እየሰራ ቢሆንም ሠራተኞቹ ግን በትግላቸው የወያኔን መረብ በመበጣጠስ እስከ አሁን ድረስ ያሉ ቢሆንም በርካታ ለአፍሪካና ለሌላው አለም መመኪያ የሚሆኑ ምሁራኖች እየለቀቁ ወደ ውጭ ሀገር እየተሰደዱ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

በሀገሪቱ ገንዘብ የለም እያሉ መልሰው በብድርና በእርዳታ የሚገኘውን ገንዘብ እየዘረፉ በውጭ ሀገር እያከማቹ ያሉት የወያኔ ባለሥልጣናት አሁን ደግሞ በአዲስ መልክ ከህዝቡ ላይ የመዝረፊያ ስልት ነድፈው እየተንቀሳቀሱ መሆኑ ታወቀ።

ሰሞኑን በሀገሪቱ ውስጥ ተሰራጭቶ ያለው የሞቦይል ካርድ 368 ብር ተገዝቶ ብዙም ሳያገለግል ተቃጥሏል በሚል መልሰው ያንኑ በምስጢር በ25 ብር እየሸጡ ህዝቡን እያማረሩ እንደሚገኙ ተዘዋውሮ ከታዘበው ዘጋቢያችን ለማወቅ ተችሏል።

ያለምንም እክል የተንቀሳቃሽ ስልኩን ከዋናው መቆጣጠሪያ ቦታ ይዘጉትና ለማስከፈት ወደ ቴሌ ሲገቡ መልሰው ያንኑ ካርድ ሰጥተው ተቃጥሎ ነበር ተከፍቷል በማለት 25 ብር ከእያንዳንዱ ሰው ላይ ገንዘብ እየሰበሰቡ ሲሆን በአሁን ሰዓት የአዲስ አበባና የክፍለ ሀገር የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ ሰዎች እያማረሩ እንዳሉም ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አስረድቷል።

ወያኔ ከሕዝብ ይልቅ ገንዘብን ከሀገር ይልቅ ሀብትን ስለሚወድ በአሁን ሰዓት በህዝቡ ላይ እየሰራ ያለው በደልና ግፍ አልበቃ ብሎት የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች ላይ የከፈሉበትን ስልክ መልሶ 25 ብር እየከፈሉ እንዲወስዱ ማድረጉ

አሳፋሪና አሳዛኝ ነው እያሉ በርካታ ዜጐች እያማረሩ መሆናቸውን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አስረድቷል።

ሌላው የሰሞኑ የሀገራችን መነጋገሪያ ርዕስ የሆነው በመላው ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ለዘመናት ተጠብቀው የኖሩት ደን መጋየት መሆኑ ነው።

በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በጐንደር፣ በሸዋ፣ በሐረር፣ በባሌ፣ በደቡብ በአጠቃላይ ዙሪያውን ደኖች አሉበት የተባሉት ቦታዎች በሙሉ በተቀነባበረና በታቀደ ሁኔታ ቃጠሎው እንዲካሄድ ሆን ተብሎ መፈፀሙን የግብርና እና የአዝርዕት ማስፋፊያ ባለሙያዎች እየገለፁ ይገኛሉ ።

እስከ ዛሬ ድረስ በጋ ወቅት ላይ የደኖች መድረቅ እሳት ለመፍጠር የሚያስችሉባቸው ሁኔታዎች ነበሩ። ነገር ግን በደጋ አካባቢ ሆን ተብለው ካልተለ ኮሱ በስተቀር ይህን የመሰለ በኪሎ ሜትር የሚቆጠር የሰደድ እሳት ሊከሰት አይችልም ። በመሰረቱ አሁን እንዳለን መረጃ ሁሉም ተቃጠሉ የተባሉት ደኖች በአንድ አቅጣጫ ሳይሆን በተለያዩ አቅጣጫዎች ነው እሳት ቃጠሎው የሚነሳው። ስለዚህ ይህ በባለሙያ አይን ሲታይ አሁን እያየንና እየሰማነው ያለው ግን ለማመን የሚከብድ ሆን ተብሎ ቃጠሎ እንዲነሳ የተደረገ ይመስላል ብለዋል።

በሰሜን ሸዋ ጣርማ በር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ከዓመት ዓመት በአካባቢው ጉም ጠፍቶ አያውቅም ታዲያ እንዴት ሆኖ ነው ቃጠሎ ሊነሳ የሚችለው? ይህ የማይታመን ነው ስለዚህ ወደፊት ሀቅ ይወጣል ሲሉም ያላቸውን መረጃ ይፋ አድርገዋል።

የሚገርመው ይላሉ እኚሁ ባለሙያ በሀገራችን እጅግ በጣም በርካታ ቦታዎች በተመሳሳይ ቀን ቃጠሎ ተነስቶባቸው እየወደሙ መሆኑ እየታወቀ አልፎ ተርፎ ገደማት ሊነዱ በተቃረበበትና ህዝቡም በተጨነቀበት ስዓት የወያኔ ሚዲያ ትንፍሽ አለማለቱ ከጀርባው ያዘለውን ተልዕኮ ማመዛዘንና መገመት አይከብደም ሲሉም ይገልፃሉ።

ዛሬ በአሰቦት ገዳም ከገዳሙ 200 ሜትር ርቀት ላይ እየነደደ ነበር፣ ዝቋላ አቦ ሙሉ በሙሉ ወድሟል፣ ዋልድባ ጋይቷል ጐንደር ውስጥ ባሌና ሻኪሶ ቀድሞ ነድዶ አልቋል። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ አንድም የእምነት አባት ነን የሚሉ ሀገርን እንመራለን የሚሉ ሆድ አደሮች ትንፍሽ ያለማለታቸው ከነመለስ ጋር ሴራውን ነድፈው የጨረሱ ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታልም ይላሉ።

የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ እንዲሉ ባሳለፍነው ሁለት ወር ውስጥ በሀገሪቱ አሉ የተባሉ ደኖች ሲወድሙ ዝም ያለው ወያኔ ሰሞኑን በሁሉም አካባቢ ደኑን ያቃጠሉ ናቸው በሚል ሀሰተኛ የፈጠራ ወንጀል

እየለጠፈባቸው በርካታ ዜጐች ለእስር እየተዳረጉ እንደሚገኙ ከተለያዩ አካባቢ የሚደርሱን ዘገባዎች ገለፁ::

በአማራ ክልል እና በኦሮሚያ ክልል ተብሎ በወያኔ ቡድን በተከለሉት ግዛት ውስጥ ለብዙ ዘመናት ሲጠበቁ የነበሩ ደኖች የወደሙ ሲሆን፣ በእልህና በቁጭት እንባ እየተናነቃቸው እሳቱን ለማጥፋት ጥረት ሲያደርጉ የነበሩትን የየአካባቢው ተወላጆች ወያኔ ደኑን ያቃጠላችሁት እናንተ ናችሁ በሚል እያፈሰ በየእስር ቤቱ እያጐራቸው መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በሰሜን ሸዋ ጣርማ በር ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ ደኑ ሲቃጠል እሳቱን ለማጥፋት ቤተሰቦቻቸውን ጭምር ሲያደክሙ የሰነበቱትን አባወራዎች መልሶ እያፈሰ በደብረሲና ከተማ እስር ቤት ውስጥ እያጐራቸው መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

በተለይ በዚህ በአማራ ክልል ውስጥ በጐንደርም ሆነ በጣርማ በር አካባቢ ደኑን አቃጥላችኋል ተብለው እየታሰሩ ያሉት ንፁህ ኢትዮጵያዊያኖች በ1997 ዓ.ም የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ ናችሁ ተብለው ታስረው የተገረፉትን እየመረጡ እያሰሯቸው መሆኑን ገልፀው አሁንም ወያኔ እራሱ ለፈፀመው ወንጀል ሕዝቡን እያሰቃየ መሆኑን ያሳያል ሲሉም አስረድተዋል::

በተመሳሳይ በምዕራብ ሐረርጌ አሰቦት ገዳም እና በደብዘረይት አካባቢ ዝቋላ አቦ ወያኔ እራሱ የለኮሰው መሆኑ የሀገሪቷ ህዝቦች ያወቁት ቢሆንም አይን አውጣው ወያኔ ግን ከዚህ ቀደም በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊነት ተስረው የነበሩትን የአካባቢው ነዋሪዎች እያፈሰ በደብረዘይትና በአሰበ ተፈሪ እስር ቤቶች እያጐራቸው እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል::

ወያኔ ዙሪያውን ታጣቂ የተቃዋሚ ኃይሎች እየጠነከሩበት ሲመጡ መምቻ ይሆነኛል በሚል እራሱ ደኖችን እያወደመ መልሶ ህዝቡን ማሰቃየቱ የነደፈው ስልት ሁሉ ጅልና የጅል ጅል መሆኑን ያረጋገጠ ነው ሲሉ አንዳንድ የግብርና ባለሙያዎች በቁጭት ሲገልፁ ተደምጠዋል::

በሰው ምድር በማይመለከታቸው ጦርነት ውስጥ እየተማገዱ ወታደሮችን የወያኔው አረመኔው ቡድን በቅኝት ላይ የነበሩትን እንደረሸናቸው በወቅቱ የአይን እማኝ የነበሩትን ጠቅሰው የመከላከያ ምንጮቻችን ገለፁ::

ባለፈው ዓመት ሰኔ ወር ውስጥ በሞቃዲሾ ውስጥ በጥበቃ ላይ የተሰማሩ የወያኔ ወታደሮች ላይ የሱማሌ አማፂ ቡድን በሞርታርና በመትረየስ ከባድ ጉዳት በማድረሳቸው የተነሳ ለስለላ ወደተለያዩ አቅጣጫ ከተላኩት 11 ወታደሮች መካከል 4ቱን ውዲያው እንዲረሸኑ መደረጉን ምንጮቹ የአይን እማኞችን ዋቢ አድርገው ገልፀዋል::

በወያኔው የጦር አዣዥ ብርጋዴየር ጄኔራል ስዩም ሀጐስ ትዕዛዝ ግድያው የተፈፀመባቸው ሲሆን የተቀሩት 7ቱ ደግሞ ለተወሰነ ቀናት ታስረው እንደነበርና አሁን የት እንደደረሱ እንደማይታወቅ ገልፀው በወታደሮቹ ላይ የሞት እርምጃ እንዲወሰድባቸው የተደረገው አስራ አንዱ ወታደሮች ቃኚዎች ስለሆኑ ለቅኝት (ለስለላ) ተልከው አቅጣጫቸውን ስተው ወደ ሌላ አካባቢ ገብተው እንደነበርና በዚህ መሀከልም የሱማሌ አማፂ ቡድን ከፍተኛ ጥቃት ሰንዝሮ በወያኔ መኮንኖች ላይ ጉዳት በማድረሱ የተነሳ ወታደሮቹ የተረሸኑ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል።

ወታደሮቹ የካርታ ትምህርት ባለመቻላቸውና ቅኝት የተላኩበት ሰፈር መንገዱን ስተው ወደ ሌላ አቅጣጫ በመሄዳቸው የተሰጣቸውን የስለላ ተግባር ሳይወጡ በመቅረታቸውና ከሄዱበት ሳይመለሱ ለአንድ ቀን በረሀብና በድካም ሲንገላቱ ውለው ሲመለሱ የወያኔው የጦር አዛዥ ስዩም ሀጐስ በወሰደው እርምጃ እንዲረሸኑ ትዕዛዝ መስጠቱን ከጊዜ በኋላ የታወቀ መሆኑን የአይን እማኞቹን ዋቢ ያደረገው ዘገባ ገልፆ በወቅቱ ሁኔታውን የተረዱ በርካታ ወታደሮች ወደ የመን በጀልባ ተሳፍረው የከዱ መሆኑንና አሁንም ባገኙት አጋጣሚ እየከዱ መሆኑን በዝርዝር አስረድቷል።

ወያኔ ለራሱ ፖለቲካ ማስፈፀሚያ ሲል ብቻ ወታደሮቹን በሱማልያ አስገብቶ ከማስፈራራቱም በተጨማሪ በሚፈጠሩ ጥቃቅን ስህተቶች ክቡር የሰው ሕይወት የሆነውን የገዛ ራሴ ናቸው በሚላቸው ወታደሮች ላይ ይህንን የመሰለ ዘግናኝ ተግባር የሚፈፅም ከመሆኑም ባሻገር እስከአሁን ድረስ ታስረዋል የተባሉት ወታደሮች በሕይወት ይኑሩ አይኑሩ የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

ደርግ ያሻውን በአደባባይ እየገደለ የፍየል ወጠጤን እየለፈፈ ሲሆን፣ ወያኔ ግን የራሴ ናቸው የስርዓቱ ማራዘሚያ ናቸው የሚላቸውን ወታደሮች ጭምር እየረሸነ ምንም እንዳልፈፀመ ሆኖ መታየቱ የስርዓቱን አረመኔነትና ጨካኝነት በጉልህ ያሳየ ነው ሲሉ የአይን እማኞቹን ዋቢ ያደረጉት ምንጮች አስረድተዋል።

ወያኔ ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት እያለ እነ አሜሪካ ወደፈለጉበት እሳት ጦሩን እንዲማግድ ትዕዛዝ ሲሰጡት ያለምንም ማቅማማት እየማገደ ሲሆን በሱማልያ የከተተው ጦር መግቢያ መውጭያ አጥቶ በየቀኑ የአማፅያኑ ጥቃት ሰለባ ሆኖ እንደሚገኝ የአለም አቀፍ ዘገባዎች እየገለፁ ይገኛሉ።

የሱማልያ የሽግግር መንግስት ተብየው ቡድን እራሱን ከማጠናከር ይልቅ በየጊዜው እየተዳከመ ከመሆኑም ባሻገር በሞቃዲሾ በአሁን ወቅት ከመቼውም ጊዜ በላይ የፀጥታው ሁኔታ አስጊ ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ ባለፈው ሳምንት

የወያኔው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን ድንገት ሞቃዲሾ እንደተገኘ አማፅያኑ የሞተር ጥቃት ሰንዝረውበት እንደነበርና ተደብቆ እንደገባው ተደብቆ ተደብቆ ለመውጣት እንደተገደደ በሞቃዲሾ የሠላም አለመኖር ማሳያ ነው ሲሉም ዘገባዎች ያስረዳሉ፡፡

በሌላ ዜና የወያኔ አጋር ነች እያለ ሻዕቢያ የሚወነጅላት አሜሪካ ሰሞኑን ዜጐቿ ወደ ኤርትራ እንዳይሄዱ ከሄዱም ከአስመራ እንዳይርቁ ስትል በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኩል ማስጠንቀቂያ አስተላለፈች፡፡

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሰሞኑን ዜጐቿ በኤርትራ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ጥሪ ማስተላለፏ በአሁን ሰዓት በወያኔና በሻዕቢያ በኩል ያለው ፍጥጫ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን በማጣቀስ መሆኑንም ጥሪው ይገልፃል፡፡

እስከዛሬ ድረስ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ነገሩ እየለዘበ መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገልፁ እንደነበር ያስታወሱት ወገኖች ዛሬ ድንገት የወያኔና የሻዕቢያ የድንበር ፍጥጫ ተካርሮ ያለበት ወቅት መሆኑን መግለፃቸው የጦርነቱ መጀመር አስመልክቶ የመሀል ዳኛ በመሆን ፊሽካ ለመንፋት የተዘጋጁ ያስመስልባቸዋል ሲሉም አሜሪካኖችን ይተቻሉ፡፡

የአሜሪካና የሻዕቢያ ቡድን ካላቸው አለመግበባት የተነሳ በአሜሪካ ውስጥ የነበሩ 2 የሻዕቢያ ቆንፅላ ጽህፈት ቤት እንዲዘጉ የተደረገ ሲሆን፣ አሁን የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ባወጣው መግለጫ መሠረት ከሆነ ጦርነቱ በማንኛ ውም ሰዓት ሊጀመር እንደሚችል ፍንጭ የሰጠ ነው ሲሉ በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች ስጋታቸውን እየገለፁ ይገኛሉ፡፡